# አደብ ቢይዝ ይበጃል

ኢብሳ ነመራ 03/27/14

ሰማያዊ ፓርቲ ሰሞኑን “የቀለም አብዮት መሪ ነኝ” እያለ እያቅራራ ነው። በቅርቡ ማሳተም በጀመረው “ነገረ ኢትዮጵያ” በተሰኘ ጋዜጣ ነው የሚያቅራራው። ሰላማዊ ትግል የሚል ሽፋን የተሰጠው ግን አንዳችም ሰላማዊ ባህሪ የሌለው የቀለም አብዮት በአጭሩ ሕገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ የመንግስት ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ የሁከት እንቅስቃሴ ነው። ይህ “ሰላማዊ ትግል” የተሰኘው በሕገወጥ መንገድ መንግስትን የመለወጥ እንቅስቃሴ የምዕራባውያን በተለይ አሜሪካ ተፅእኖዋን በአለም የምታስፋፋበት ስልት ነው። ዓላማው የመንግስት ለውጥ ለማድረግ የተመረጠውን ሀገር ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ሰላምና ብልፅግና ማረጋገጥ ሳይሆን የአሜሪካና የተከታዮቿን ምዕራባውያን አገራት የበላይነት ማስጠበቅ ነው።

ይህን ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ለማካሄድ በአሜሪካ መንግስት የተቋቋሙና የገንዘብ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (Governmental Non Governmental Organizations) ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህ መሃከል፣ (National Endowment for Democracy/NED) ብሄራዊ ኢንዶውመንት ለዴሞክራሲ ናሽናል፣ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ ተቋም (National Democratic Institute for International Affair/NDI)፣ ዓለም አቀፍ የሪፐብሊካን ኢኒስቲቱት (International Republican Institute/IRR)፣ ዓለም አቀፍ የምርጫ ሥርአት ፋውንዴሽን (International Foundation for Electoral System/IFES)፣ ዓለም አቀፍ የጥናትና የልውውጥ ቦርድ International Research and Exchange Board/IREX)፣ ፍሪደም ሃውስ (Freedom House) ወዘተ የተሰኙት ተጠቃሾች ናቸው።

እነዚህ “መንግስታዊ ያልሆኑ” የሚል ሽፋን የለበሱ ድርጅቶች በሙሉ የአሜሪካንና ከዚሁ ጋር በተያያዘ የምእራብ አውሮፓ አገራትን ተፅእኖ በዓለም ላይ በማስፋፋት የአገራቱን 90 በመቶ ሃብት የተቆጣጠሩ ከአጠቃላይ የአገራቱ ሕዝብ ጋር ሲነፃፀሩ ከ1 በመቶ ብቻ የሆኑ ፈላጭ ቆራጭ ባለፀጎች (financial oligarchy) ጥቅም ማስጠበቅ ነው። የአሜሪካና

የምእራባውያን ፖለቲካ በእነዚህ የህዝባቸውን 1 በመቶ በሚሆኑ ፈላጭ ቆራጭ ባለፀጎች (financial oligarchy) እጅ ነው ያለው። እነርሱ ያልወደዱት ወደ ስልጣን አይመጣም፡፡ እንዳጋጣሚ ወደ ስልጣን ቢመጣም የእነርሱን ጥቅም ከማስፀም ያለፈ ጉልበት እንዳያገኝ ያደርጋሉ።

ባለፀጎቹ መንግስት ኢኮኖሚውንም ሆነ ሌላ የህዝቡን ማህበራዊ ጉዳይ መደጎም የለበትም የሚል አቋም ነው ያላቸው፡፡ እነርሱ መደጎም ከፈለጉ ግን መንግስት እንዲደጉም ማድረግ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ፕሬዝዳንቱ ለጤና አገልግሎት የጠየቀው ባጀት አልተፈቀደም። ይህ አነስተኛ ገቢ ያላቸው አሜሪካውያንን የሚደጉም ባጀት ነበር። ይሁን እንጂ አሜሪካ በገንዘብ ቀውስ የተመታች ግዜ ባለጠጎቹ ስለተጎዱ ባንኮቻቸውና የመኪና ፋብሪካዎቻቸው እንዲደጎሙ ማድረግ ችለው ነበር።

አሜሪካን ጨምሮ በምእራባውያን አገራት ሕዝቡን በረቀቀ ስልት ከፖለቲካ ውጭ ስላደረጉት የምርጫ ተሳተፎው አነስተኛ ነው። በተለይ በአሜሪካ አብዛኛው ሕዝብ እንኳን መሪውን ሊመርጥ፣ መሪው ማን እንደሆነ የማያውቅበት ሁኔታ ነው ያለው። የምእራባውያን "ዴሞክራሲ" በአጭሩ ይህን ይሚመስል ነው።

እንግዲህ ሰማያዊ ፓርቲ "ይገፋላችሁ መጣሁ" እያለ የሚያቀራራው የቀለም አብዮት፣ ምእራባዊያን የሌሎችን አገር ተቆጣጥረው የባለፀጎቻቸውን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ የሚከተሉትን ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴ ነው። ልብ በሉ ይህ የሰማያዊ ፓርቲ አካሄድ ከድህነት ለመውጣት የሚፍጨረጨረውንና በተለይ ከጥቂት አመታት ወዲህ ተስፋ እየታየው የመጣውን የኢትዮጵያ ህዝብ ታሳቢ ያደረገ አይደለም። የቀለም አብዮት በአጭሩ ዘመናዊ የጭኝ አገዛዝ ስልት ነው። ሕዝብ በምርጫ የስልጣን ውክልና የሰጠውን መንግስት ጥቂቶች በተሳተፉበት የጎዳና ለውጥ በሕገወጥ መንገድ በማስወገድ ደደብ የምእራባውያን አሻንጉሊቶች ስልጣን ላይ እንዲወጡ የሚደረግበት ስልት ነው።

የቀለም አብዮት በበርካታ አገራት ተሞክሯል። በምስራቅ አውሮፓ፤ አ ኤ አ በ2003 በጆርጂያ የተሞከረው የሮዝ አብዮት፣ በ2004 በዩክሬይን የተሞከረው ብረቱካናማ አብዮት፣ በ2005 በኪርጊስታን የተሞከረው ሃምራዊ አብዮት ተጠቃሾች ናቸው። በኢስያ አገራትም፣

በሊባኖስ፣ ኩዌት፣ ኢራን ወዘተ የተለያየ የቀለም መለያ የተሠጣቸው አብዮቶች ተሞክረዋል። አብዛኞቹ ግን የተፈለገውን የአሜሪካን የበላይነት የሚያረጋግጥ ሁኔታ መፍጠር አልቻሉም። የተወሰኑት በቀለም አብዮት ወደ ስልጣን የመጡ መሪዎች የምእራባውያን ታማኝ አሻንጉሊቶች ከመሆን ያለፈ የመሪነት ብቃትም ስነምግባርም የሚጎላቸው ስለነበሩ በቀጣይ ምርጫ ህዝቡ ከስልጣን አስወግዷቸዋል። የተቀሩት አብዮቶችም ከጎዳና ላይ ጫጫታነት ሳያልፉ ከሽፈዋል።

እስካሁን ግብፅና ሶሪያን እያመሳቸው ያለው ሁኔታ የተፈጠረው ምእራባውያን የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ባቀናበሩት የቀለም አቢዮት  የመንግስት ለውጥና የመለወጥ ሙከራ ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው በሁለቱም አገራት ደም ያፋሰሰ እልቂት፣ የኢኮኖሚ ድቀት በማምጣት ዜጎችን ለስቃይና ለመከራ ከመዳረግ ያለፈ ፋይዳ ያለው ለውጥ አላመጣም።

ከሕዳር ወር ጀምሮ በምስራቃዊቷ አውሮፓ ሀገር ዩክሬይን የተካሄደው በአሜሪካ የተመራ ሕገ ወጥ የመንግስት ለውጥ የተሳካ መስሎ የነበረ ቢሆንም፣ ራስ ገዝ የነበረችው ክሪሚያ የተሰኘች ግዛት ዜጎች፣ ነፃነታቸውን ለማስከበር በያዙት አቋም ግዛቲቱ  ከ97 በመቶ በላይ ድጋፍ ባገኘ ሕዝበ ውሳኔ ተገንጥላ ከሩሲያ ፌዴሬሽን ጋር ተቀላቅላለች። ምእራባውያኑ በክሪሚያ ነፃነት ሩሲያን ቢኮንኑም የመገንጠሏ ምክንያት ተፅእኗቸውን ወደ ምስራቅ አውሮፓ ለማስፋፋት በማሰብ በዩክሬን ከምርጫ ውጭ በሕገወጥ መንገድ የመንግስት ለውጥ እንዲካሄድ ማድረጋቸው ነው፡፡ ምዕራባውያኑ በጎዳና ላይ ነውጥ ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ማካሄድ ያስፈለጋቸው የእነርሱን ፍላጎት የሚያስጠብቁ  አሻንጉሊቶች  በምርጫ የአብላጫ ሕዝብ የስልጣን ውክልና እንደማያገኙ የሚያውቁ መሆናቸው ነው።

ሕገወጥ የመንግስት ለውጡ ያስከተለው የክሪሚያ ተገንጥሎ ከሩሲያ ጋር መዋሃድ ያደናገጣቸው ምዕራባውያን የክሪሚያን ሕዝበ ውሳኔ ሕገወጥ ብለውታል። ልብ በሉ ከ97 በመቶ በላይ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ ያገኘን ሕዝበ ውሳኔ ነው ሕገ ወጥ የሚሉት። ምእራባውያኑ በተለይ በአሜሪካ "መንግስታዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች" አማካኝነት በተደራጁ ጥቂት የከተማ አዋኪዎች ግፊት የተካሄደውን የመንግስት ለውጥ ግን እንደተገቢና ሕጋዊ ነው የቆጠሩት። ይህ የቀለም አብዮት የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት

ያላገናዘበ የአሜሪካ ባለፀጎችን ጥቅምና ፍላጎት ማሟላትን ብቻ ያለመ ከቅኝ ግዛት ስርአት አካሄድ ያልተለየ መሆኑን በተጨባጭ ያረጋግጣል።

የቀለም አብዮት እንቅስቃሴ ወደ ህዝብ ለመግባት የሚከተላቸው ስልቶች አሉ። ከእነዚህ ስልቶች መሃከል ሕዝብን ሊያነሳሳ የሚችል ቀውስ መፍጠርና የተፈጠሩ ቀወሶችን ያለአግባብ ማራገብ፣ ምጥጫ ቦርድ፣ ፍርድ ቤት የመሳሰሉ ተቋማት በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጡ የፈጠራ ወሬዎች በመንዛት ማጣጣል፣ የምእራባውያን አሻንጉሊት ለመሆን የተዘጋጁ አዙረው ማሰብ የማይችሉ ደደብ ሰዎችን  የተለያዩ ሽልማቶችን በመስጠት ስብእናቸውን መካብ ተጠቃሾች ናቸው። ለአሻንጉሊትነት ለተዘጋጁት ግለሰቦችና ላደራጁት ፓረቲ፣ ደጋፊዎቻቸው ለመሆን ፍቃደኛ ለሆኑ ፕሬሶችና ጋዜጠኞችም ሞቅ ያለ የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

የቀለም አብዮት አብላጫ ቁጥር ባለው ሕዝብ የሚካሄድ ሳይሆን በከተማዎች አካባቢ በተፈጠሩና ያለወጉ በተራገቡ ቀወሶችና ተያያዥ ሁኔታዎች ተደናገረው ለተቃውሞ በተነሱ ጥቂት ስሜታዊ ሰዎች ነው።  የቀለም አብዮት አስፈፃሚ ፓርቲዎች ምርጫን ሕዝብን ለማነሳሳት እንጂ ተፎካክሮ ለማሸነፍ አይጠቀሙበትም። የዚህ አይነት ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴን የሚመርጡትና ይህን ለማስፈጸም ከአሜሪካ “መንግስታዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች” ተልዕኮና ገንዘብ የሚሰጣቸው ፓርቲዎችና አመራሮች የአብላጫ ሕዝብ ይሁንታ  የሌላቸው፣ በህዝብ ውክልና ስልጣን ላይ የመውጣት ተስፋ የሌላቸው ናቸው።

እንግዲህ ሰማያዊ ፓርቲ ከዚህ አይነት ፓርቲዎቸ አንዱ ነው። ፓርቲው በቅርቡ ማሳተም በጀመረው ጋዜጣው (የፓርቲው ልሳን ይሁን ነፃ ጋዜጣ በውል አይታወቅም) በኢትዮጵያ የቀለም አብዮት የመምራት ሃላፊነት እንደተሰጠው እየነገረን ነው። በመጋቢት 12/2006 ዓ/ም የነገረ ኢትዮጵያ ዕትም ላይ የፓርቲው ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነት በአሜሪካ መንግስት መመረጣቸውነና መሸለማቸውን ኢትዮጵያዊ ቁጥብነት በጎደለው ጉራ የተናገሩትን አንብበናል። ራሳቸውን እያዋደዱ የሌላቸውን ስብእና ለመፍጠር ነው ይህን ያደረጉት።

ሰማያዊ ፓርቲ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ አንዴም ስለምርጫ፣ ስለሥልጣን ውክልና አውርቶ አያውቅም። ለምርጫ የሚቀርብ አማራጭ ፖሊሲና አቋምም አስጨንቆት አያውቅም። ይህ የሆነው በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የሕዝብን ይሁንታ አግኝቶ ስልጣን በውክልና መረከብ እንደማይችል ስለሚያውቀውና ለዚህ ዝግጅት የማድረግ አቅምም ፍላጎትም ስሌለው ነው።

ፍላጎት ያጣው ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት የሆኑበትን፣ ባመቻቸውና በመከባበር በእኩልነት የሚኖሩበትን አዲሲቱን ፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ስለማይቀበል ነው። ይህን ስርዓት ተፃርሮ በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የስልጣን ውክልና ማግኘት እንደማይቻል ስለሚያውቅ፣ ከምርጫ ውጭ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ስልጣን መያዝ የሚያስችል ማንኛውንም አማራጭ ለመቀበል ተዘጋጅቷል።

እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ከቅኝ ግዛት ባልተለየ ሁኔታ የራሳቸውን ጥቅም ከማስጠበቅ ውጭ ለየትኛውም አገር ሕዝብ፣ ዴሞክራሲ፣ ሰላምና ብልፅግና ደንታ በሌላቸው በምዕራባውያን የገንዘብ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ የሕወጥ የመንግስት ለውጥ አቀናባሪዎች ሰማያዊ ፓርቲን ሊያጩ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ያመለክታሉ።

ሰማያዊ ፓርቲ በብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የተዋቀረችውን አዲሲቱን ፌደራላዊት ኢተዮጵያ ማስተዳደር የሚያስችል አወቃቀር የለውም። አዲስ አበባ ከተማ ላይ ከአባቶቻቸው አሮጌ አመለካከት የወረሱ ጥቂት አዛውንት ወጣቶች የታጀበ፣ የአንድ ቋንቋና ባሕል የበላይነት የሰፈነባት አሃዳዊ ኢትዮጵያን የመመስረት ቅዠት ውስጥ ያለ ፓርቲ ነው። የሰማያዊ ፓርቲ በሚያሳትመው ነገረ ኢትዮጵያ የተሰኘ ጋዜጣ ላይ የሚወጡ ፅሁፎች ይዘት፣ "ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያየ መገለጫና ማንነት ያላቸው ብሄሮች የሉም፣ ያለው አንድ ኢትዮጵያ የተሰኘ ብሄር ነው" የሚል ቃና ያላቸወ ናቸው።

ለአብነት ያህል በነገረ ኢትዮጵያ የመጋቢት 12 ዕትም "መዝሙረ ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ የቀረበ ፅሁፍ ላይ " . . . 'የጋራ የተዛመደ ህልውና ያለን ብለው የሚያምኑ' ማለት ምን ማለት ነው? ኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና የለንም ማለት ነው እንዴ?" በሚል የሰፈረውን ሃሳብ ለዚህ ማሳያነት መጥቀስ ይቻላል። "የራሳቸው ማንነትና

መለያ ያላቸው ብሄሮችና ብሄረሰቦች የሉም" እያለ መሆኑን ልብ በሉ። ይህ ሁኔታ ሰማያዊ ፓርቲ ለኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የሰጠውን ስፍራ ያሳያሉ።

ሰማያዊ ፓርቲ በዚህ አቋሙ ምክንያት በኢትዮጵያ ሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ኦሮሚያ …. ክልሎች የስልጣን ውክልና ሊያገኝ አይችልም። ክልሎች ካልወከሉት ደግሞ የፌዴራል መንግስቱን ስልጣን መረከብ የሚያስችል አንዳችም መንገድ የለም። ለነገሩ በእነዚህ ክልሎች ለመወዳደር የሚያስችለው አደረጃጀትም አባላትም የሉትም።

ሰማያዊ ፓርቲ አሁን ባለው አቋሙ በክልሎች ቢወዳደር እጩዎቹ ለየብሄሩና ብሀረሰቡቹ የሚያቀርቡት አማራጭ "በቋንቋህ እንዳትናገር፣ እንዳትሰራ፣ ልጆችህን እንዳታስተምር፣ አደርጋለሁ፤ ባህልህን እንዳታሳድግ፣ ራስህን በራስህ እንዳታስተዳድር አደርጋለሁ" የሚል አማራጭ ከመሆን ውጭ እንዳልሆነ እንደሆነ ልብ በሉ። ይህ የአማራጭ አቋም ምን እንደሚያሰከትል ደግሞ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

ሰማያዊ ፓርቲ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት፣ በአሜሪካ "መንግስታዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ያልሆኑ ድርጅቶች" ድጋፍ የሚካሄድ የቀለም አብዮት የተሰኘ ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ወደ ስልጣን ለመውጣት የሚቅበዘበዘው ከላይ በተገፀፀው ሁኔታ በምርጫ የማሸነፍ አንድም ተስፋ ስለሌለወ ነው። ሰማያዊ ፓርቲና ደጋፊዎቹ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳደሩ፣ የፌዴራል መንግስቱም የስልጣን ባለቤት የሆኑ ዘጠኝ ክልላዊ መንግስታት ያልተማከለ የመንግስት ስርአት በመሰረቱበት ሁኔታ ጥቂት ስሜታዊ ሰዎች አዲስ አበባ በሚንጫጩበት የቀለም አብዮት መንግስትን አስወግዶ ስልጣን መያዝ እንደማይቻል መገንዘብ አለባቸው።

አዲስ አበባ ላይ ጥቂቶች ጎዳና ላይ ወጥተው የሚፈጥሩት ሁከት "በሆነ መለኮታዊ ተአምር የፌዴራል መንግስቱን ሊያስወግድ ይችላል" የሚል እምነት እንኳን ቢኖር ኢትዮጵያን የገነቡት ክልሎች ከላይ ወደታች ስለማይመሩ የየራሳቸውን ክልል ይዘው ነው የሚቀሩት። በኃይል ስልጣን ላይ የወጣው አካል ምንም የሚገዛው ነገር ሳይኖረው አየር ላይ ነው የሚቀረው። እናም የሰማያዊ ፓርቲ የቀለም አብዮት ሙከራ እንዳጋጣሚ ሊሳካ ይችላል ተብሎ ቢታሰብ እንኳን ሀገሪቱን ከመበተን ያለፈ የሚያመጣው ነገር አይኖርም።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ መንግስትን በኃይል ለማስወገድ መሞከር ሃገሪቱን ለመበተን ካለ ፍላጎት ብቻ ነው ሊመነጭ የሚችለው። ኢትዮጵያን መበታተን ደግሞ ጥንካሬዋ ያልተመቻቸው የሸአቢያና መሰል ታሪካዊ የኢትዮጲያ ጠላቶች ፍላጎት ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያን ሊያፈራርሱ የሚፈልጉ አካላት ከእነዚህ የኢትዮጲያ ታሪካዊ ጠላቶች ተላላኪነት ለይቶ መመልከት አዳጋች ነው።

በዩክሬይን በምርጫ በሚገኝ የህዝብ ውክልና ስልጣን ላይ መውጣት እንደማይችሉ የሚያወቁ በምዕራባውያን የሚደገፉ ቡድኖች ዋና ከተማዋ ኬዩቭ ላይ መንግስትን በኃይል ሲያስወግዱ የክሪሚያ ራስ ገዝ ዜጎች ምዕራባውያን ባስቀመጡት የኪዮቭ መንግስት ለመገዛት ፍቃደኛ እንዳልነበር አስታውሱ። ይህ ሁኔታ በመጨረሻ የክሪሚያን ነፃ መውጣት አስከተለ። በሌሎችም የምስራቅ ዩክሬይን አካባቢ ያሉ ራስ ገዞች ውስጥ ተመሳሳይ ዝንባሌ ያለ መሆኑንም አስታውሱ።

ምዕራባውያን የሕዝቡን ፍላጎት ችላ ብለው የጥቁር ባህርን ተቆጣጥረው ተፅእኖቻቸውን በማጠናከር ቅዠት ታውረው ያካሄዱት የቀለም አብዮት የዩክሬይንን ሕዝብ አልጠቀመውም። ለወደፊትም የምዕራባውያን ጥገኛና ጉዳይ አስፈፃሚ ከማድረግ ያለፈ ምንም እንደማይጠቀም ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

ምዕራባውያኑ የሌሎች አገር ቢጠፋም ቢለማም ምንም ግድ የላቸውም። የራሳቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት በማሳካት ታጥረው ነው የሚንቀሳቀሱት። በመሆኑም ያልተማከለ ፌዴራላዊ አወቃቀር ባለባቸው አገራት በቀለም አብዮት የመንግስት ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ እንቅስቃሴ ሊያስከትል የሚችለው የመበታተን ጥፋት አያሳስባቸውም።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ ባረጀ ባፈጨ መነፅር ኢትዮጵያን እየተመለከተ አሁን ባለው በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርአት ላይ ባደረበት ጭፍን ጥላቻ በተቃኘ የቀለም አብዮት “ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ አካሂዳለሁ” በሚል ቅዠት የሚቅበዘበዘውን ሰማያዊ ፓርቲ ከወዲሁ አደብ ሊያሲዘው ይገባል።